# ግልብ አንባቢ ግልብ ተመልካች ፤ግልብ ተመልካችም ግልብ ገምጋሚ ይሆናል!

ቀለሙ በለጠ (ባህር ዳር)

04-10-17

እንግሊዛዊው ኤድዋርድ ሞርጋን ፎረስተር እ.ኤ.አ (1879–1970) ብዙውን ጊዜ E.M Forster በመባል ይታወቃል፡፡ ስሙ-ጥር የረጅምና አጫጭር ልብወለድ ፀሀፊ ነበር፡፡ በነፃ አስተሳሰብ አራማጅነቱም ይታወቃል፡፡

በተለይም በአገራቸው አቆጣጠር በ1924 በሳተመውና ከፍተኛ ታዊቂነትን ባተረፈለት የረጅም ልብወለድ ስራው ኤ ፓሴጅ ቱ ኢንድያን ጨምሮ 16 ጊዜ የስነ-ፅሁፍ የኖቬል ሽልማት ወስዷል፡፡ ፎረስተር እጅግ የታወቀና '' የተደላደለ አዕምሮ የነበረው መፅሀፍ ሀያሲም ነበረ፡፡

በንባብ ክህሎታቸው የዳበረ ልምድ ያላቸውን የሀገሩን ወይም እንግሊዛዊያን አንባቢዎች ሳይቀር ከ ኢ.ኤም ፎርስተር የሰላ ሂስ አላመለጡም፡፡

ኢ.ኤም ፎርስተር እንግሊዛዊያን አንባቢዎችን በሁለት ይከፍላቸዋል ፡፡ Critical & Passive ብልህ እና ግልብ ወይም ለብለብ አንባቢያን እንደ ማለት ነው፡፡

ግልብ ወይም ለብለብ አንባቢያን የሚባሉት አንድን መፅሀፍ፤ ወይም የኪነ-ጥበብ ስራ እንደተጠቀሙበት የአውቶብስ ትኬት አንድ ጊዜ ብቻ አንብበው የሚጥሉ ሲላቸው ከንባብ በኋላ እዚህ ግባ የሚባል ቁም ነገር አይጨብጡም ይላቸዋል ፎርስተር ፡፡

ግልብ ወይም ለብለብ አንባቢያን አንድ የኪነ-ጥበብ ወይም ምርምር ስራ ካነባቡ በኋላ ገጠመኞችን ከመመዘን ወይም  ከመፅሀፉ ሴማና መልዕክቱ ህያው ልምድ ከመቅሰም ይልቅ ንባቡ በሚፈጥረው ስሜት ይነዳሉ፡፡

ኢ.ኤም ፎርስተር ግልብ አንባቢያን የኪነ-ጥበብ ወይም የምርምር ስራው  ለሚፈጥረው የሀዘን ወይም የደስታ  ስሜት ተቀማጭ ቀለብተኞች ናቸው ባይ ነው፡፡ Passive readers are a passive recipient of pleasures ( E.M Forester).

በተነፃፃሪ ብልህ አንባቢያን አንድን የጥበብ ስራ ሁለትና ሶስት ጊዜ ብቻ ሳይሆን አስር ጊዜ ደጋግመው ያነባሉ፡፡ በሂደትም ንባብ ከሚፈጥረው ጊዚያዊ የደስታ ወይም ሀዘን ስሜት ይልቅ የመፅሀፉን ታሪክ፣ የታሪኩ መዋቅር፣ ሴማውና መልዕክቱን ይረዳሉ፡፣ ከመፅሀፉ ገጠመኞችን መለየትና መመዘን ይችላሉ፡፡ የንባብ ክህሎት ትሩፋት የሆነውን ህያው የሆነ ልምድ መቅሰም የሚቻለው በብስለት በማንበብ መሆኑን ኢ.ኤም ፎርስተር ያብራራል፡፡

በሀገራችን በአማርኛ ቋንቋ ደራሲነቱና ሀያሲነቱ እጅግ የታወቀው ዮሀንስ አድማሱ በ1961 ፡  የልብ ወለድ ስነ-ፅሁፍ ጉዞ  በተሰኘ ርዕስ የብርሀኑ ዘሪሁን የበኩር ስራ የሆነችዋን የዕንባ ደብዳቤዎች ደግሜ ደጋግሜ አንብቤያታለሁ፡፡ ካለ በኋላ ከ10 ጊዜ በላይ አንብቢያታለሁ ይላል፡፡

የዮሀንስ አድማሱ አባባል ከኢ.ኤም ፎርስተር ምክረ-ሀሳብ ጋር ከመመሳሰሉ ባሻገር በሀገራችን ለመፅሀፍ ምረቃ ተጋብዘውና ገና ለገና የመፅሀፉ ርዕሰ-ጉዳይ በአግባቡ ሳይገባቸው የመሀፍ ዳሰሳ ለመስጠት ለሚንተባተቡት ለአይጋ ፎረሙ ደምበኛ አቶ ሲሳይ መንግስቴ አዲሱና መሰሎቹ  ጠቃሚ ምክረ-ሀሳብ ሆኖ አግኝቸዋለሁ ፡፡

በኢ.ኤም ፎርስተር ዘመን የሰለጠነው አለም የስነ-ፁሁፍ ስራ ንባቤ ቃልና ሂስ እጅግ ዝቅተኛ እነደነበር እንረዳለን፡፡ በ40 አመታት ጊዜ የተጓዘው እርቀትም እምብዛም ነው፡፡ የአንድ ምዕተ-አመት ዘመን የማይሞላ ያውም ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ህገ-መንግስታዊ ድጋፍ ከተሰጠው ገና ሁለት አስርትና ምናምን አመታት የሆነው  የሀገራችን የምርምርም ሆነ የጥበብ ስራዎች  ጉዞ ገና ድንግል ነው ማለት ይቻላል፡፡  በዚህ ወቅት አቶ አለምነው መኮነን ፖለቲካል ኢኮኖሚና የኢትዮጲያ ህዳሴ! በሚል ርዕስ መፅሀፍ አሳትሟል፡፡

 አለምነው ይህ መፅሀፍ የበኩር ስራው ይሁን እንጅ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከሚያቀርብልን የርዕዮ አለም ፤ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ጹሁፎች አንባቢን ወደ አዲስ ምዕራፍ ማሻገር የሚያስችል  አዲስ ጉልበት ይዞ መቅረቡን መረዳት ላያዳግት ይችላል ፡፡ እንደ ሲሳይ መንግስቴ አይነት ግልብ የመፅሀፍ ገምጋሚ ግን አለምነውንም ሆነ የአገራችንን ጅምር የጥበብና ምርምር ስራዎች ያቀጭጭ እንደሆን አንጅ አያፋፋም፡፡

በዚህ ዝግጅቴ በአቶ አለምነው የፖለቲካል ኢኮኖሚና የኢትዮጲያ ህዳሴ  መፅሀፍ ላይ እንደ አቶ ሲሳይ አላዋቂ ሳሚ .... አይነት.  በተለመዱና የተሰለቹ የመፅሀፍ ዳሰሳ መገለጫዎችን የሀተታ አካል አድርጎ ከማቅርብ ይልቅ የኢ.ኤም ፎረስተርን ሙያዊ ምክር ገንዘብ በማድረግ በሌላ ጊዜ በተደላደለ አዕምሮ ለመመለስ ቃል መግባትን መርጫለሁ፡፡

በዚህ ዝግጅቴ ግን ከሲሳይ ራስ አልወርድም ፡፡ ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ  በአለምነው ፖለቲካል ኢኮኖሚና የኢትዮጲያ ህዳሴ መፅሀፍ ላይ በ04/01/17 በአይጋ ፎረም የፃፉት የመፃፍ ዳሰሳ  ሚናው ምን ነበር በእርግጥስ ይህ አይነት የመፅሀፍ ዳሰሳ አቀራርብና አስተያየት ታዳጊውን የሀገራችን የስነ-ፅሁፍ ማሳ  እንዳይጎዳው ያሳስበኛል ፡፡

ምክንያቱም እንደ ኤ.ኤም ፎርስተርና የዘርፉ ባለሙያዎች ትንታኔ  የመፅሀፍ ዳሰሳ ወይም ሂስ ለስ- ነፅሁፍ ማደግ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና አንባቢን ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ማሸጋገር ከሆነ  ሲሳይ  የዓለም ፖለቲካ በአቶ አለምነው በሚል  የቀረበው  ባለ ሰባት ገፅ ምልከታ  የመፅሀፍ ዳሰሳ ወይስ ፤ የመፅሀፍ ምረቃ ዘገባ ወይስ  የጋዜጣ አዟሪ ሚና ግልፅ አይደለም ፡፡ ከአንድ የዩኒቨርስቲ 'ፕሮፌሰርም' የሚጠበቅ አይደለም ፡፡

የፖለቲካ ኢኮኖሚና የኢትዮጲ ህዳሴ የመፅሀፍ ዳሰሳ ሙያ  የሚጠይቀውን  ጠቃሚ ሀሳብ መሰንዘር ሳይቻል አሻግሮ መፅሀፍ ምረቃ ላይ ምናልባትም በተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል ብየ አስባለሁ ያልተገኙ አመራሮች ላይ ዛቻ የሚመስል አስተያየት መሰንዘር ጠቃሚ ሆኖ አላገኘሁትም ፡፡ ከመግቢያው ስጀምር ሲሳይ ከደራሲው ጋር የነበረው ትውውቅና ቅርበት ለአንቱታ የማያበቃ እንደነበር  ጠቅሶ ደራሲው አሁን ከሚገኝበት የስልጣን ከፍታ አንፀር መዘርጠጥ ስለሚሆንበት አንቱታውን መምረጡን ፅፏል ፡፡

የአንድን ደራሲ  መፅሀፍ ጠንካራና ደካማ ጎን ስንፈትሽ ደራሲውን በስሙ  መጥራት በእኔ አተያይ  መዘርጠጥ አይደለም፡፡ ሲሳይ መዘርጠጥ አለው እንጂ ደራሲ አንተ እንጅ አንቱ  አይባልም ፡፡ ምንም እንኳ የደራሲያኑ ስራ ከማህበራዊ ለውጥ አኳያ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ቢሆንም ፡፡ በዚህ ረገድ ክፍተትህን ብትፈሽ 'ፕሮፌሰር'፡፡

ይልቁንስ ክብር የሚገባውን ክብር ሳንሰጥ ስንቀር ነው ዝርጠጣ የሚሆነው፡፡ ምንም እንኳ በባህላችን አንቱ የሚባል ስራ ያበረከቱ ሰዎች አንቱ ተብለው በማይገለፅበት ቦታ አንቱ ማለትና ክብር የሚገባቸውን ደግሞ መዘርጠት ከአቅም ዕጥረት ባሻገር አድርባይነት ነው፡፡ አለምነውን እዚህ በማድረሳቸው ያልመከኑትን *የልማታዊና ዲሞክራቲክ መስመር መነኩሴዎች*!! እየዘረጠጥክ አለምነውን አከብረዋለሁ ማለት የለየለት አድርባይነትና በክህደት መንገድ መንፈስህን ያሳያል፡፡

የአቶ አለምነው መፅሀፍ ለአንባቢያን በአለም ላይ ሰራ ላይ ከዋሉትና እየዋሉ ከሚገኙት የፖለቲካ ርዕዮተ አለሞች ኢትዮጲያ ተግባራዊ የምታደርገው ልማታዊና ደሞክራሲያዊ መስመር ብቸኛ አማራጭ መሆኑን ግንዛቤ እንደሚሰጥ ሲሳይ መንግስቴ በዳሰሳው ጠቅሷል ፡፡ ይህ በጣም እሰየው ነው ፡፡

ከአንድ ወር በፊት የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በፌስ ቡክ እንቶ ፈንቶ ተረብ ከምትፅፍ ይልቅ ስለ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መንግስት ፅንሰ-ሀሳብና አተገባበር ጥናትና ምርምር ለምን አታደርግም ? በሚል ለተነሳልህ ጥያቄ 'ልማታዊ ዲሞክራሲ ማለት የአምባገነኖች መሳሪያ መሆኑን ማን' ? በነገረህ የሚል ማብራሪያ መስጠትህ ይታወሳል፡፡

ታዲያ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያውም እንደ ፎርስተር አባባል በግልብ ንባብ ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመር ብቸኛ አማራጭ መሆኑን እንዴት መገንዘብ ቻልክ ? ለምኔው ተገልብጠህ ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመር የኢትዮጲ ህዳሴ ብቸኛ አማራጭ ነው :: ከሚል ማደማደሚየ ደረስክ ? ይህ እውነት ከሆነና ከአድርባይነት ባህሪህ የመነጨ ካልሆነ እሰየው ነው፡፡ እንኳን ደህና መጣህ !!

መፅሀፍ ሲዳሰስ ወይም አስተያየት ሲሰነዘር ሲሳይ ያነሳቸው መግቢያ፣ ቋንቋ ፣ የመጽሀፉ ጭብጥ ወዘተ...የመሳሰሉ የተለመዱ መገለጫዎች የሀተታ አካል ከመሆናቸው በፊት መጻህፉን ደግሞ ደጋግሞ በማንበብ ከመፅሀፉ ርዕሰ-ጉዳይ ጀምሮ የመፅሀፉን ማዕከላዊ ጭብጥ መረዳትና ለአንባቢያን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር አስተያየት መሰንዘር ይጠይቃል ፡፡

ጠቃሚ አስተያየት ለመሰንዘር ደግሞ የተደላደለ አዕምሮ ይዞ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ የተደላደለ አዕምሮ ለመያዝ ደግሞ በለብለብ ንባብ የማይቻል መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ለመሆኑ የጥልቅ ተሀድሶ እየመራ የሚገኝን አንድ አመራር ለምን ሽራተን ወይም

ካፒታል ሆቴል አላስመረቀም የሚል አስተያየት ከአንድ ጥገኛ ቢሰነዘር ለእኔ አዲስ አይሆንብኝም ፡፡

በመፀሀፉ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ በሲሳይ እንደ ችግር የተነሱ ሀረጎችና ቃላቶች የደራሲያንን መብት ከግምት ያላስገቡ ስለመሆናቸው ምን ይህል ዕርግጠኞ ነህ ? በሂስ ጥበብ ቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ  ይህን ቃላት ወይም ሀረግ አትጠቀም ከማለት ይልቅ ይህን ቃል ወይም ሀረግ ብትጠቀም ኑሮ ጎደሎውን የተሟላ ያደርገዋል እንጂ ለምን እንግሊዝኛ ቃላትን አየሁ የሚል ሀሳብ መሰንዘር መፅሀፍ ዳሰሳውን የተሟላ አያደርገውም ፡፡

በአጠቃላይ ግልብ አንባቢ ከስሜት ወጥቶ ለጥበብ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለሚያበረክተውና  ስርዓት ባለው መልክ የስነ-ፅሁፍም ሆነ ምርምር ስራን መመዘን ብሎም ጥበብ እያደር የሚያብብበትን ስልት መቀየስ ለሚያስችለው የመፅሀፍ ዳሰሳ/ሂስ ብቃት ሊኖረው አይችልም ፡፡

ግልብ አንባቢ መሆን ግልብ ተመልካችነትና ያመጣል፡፡ ግልብ ተመልካችነት ደግሞ ወደ ግልብ ገምጋሚነት እንዳይጋብዘን ጥንቃቄ እናድርግ፡፡